በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፮ አምላክ አሜን። ለቅዱሳን የተሰጠ ቃል ኪዳን መስከረም ፲፰ ቀን ተጀመረ።

፩ኛ አቡነ ቶማስ

የሚገኙበት ቦታ ሽሬ አውራጃ እንደባጉና ከተማ ወጣ ብሎ የእረፍታቸው ቀን ጥር ፳፭ ከዚህ ቦታ ከሩቅም ሆነ ከቅርብ መጥቶ በዓልህን ያከበረ እስከ ፳ ትውልድ እምርልሃለሁ፡ እመቤታችንም በቀን ፭ ጊዜ በየ፫ ሰዓት እየመጣሁ እስከ ዕለት ምጽአት ድረስ ቦታህን እባርከዋለሁ ብላ ቃል ኪዳን ገብታላቸዋለች።

፪ኛ አቡነ አረጋዊ

የሚገኙበት ቦታ በሰሜን ምዕራብ አዲግራት ከተማ የተሰወሩበት ቀን ጥቅምት ፲፬ አቡነ አረጋዊ ከእንጦንስ እና ከመቃርስ ከጸኩሚስም የምንኩስና ወይም መንፈሳዊ ሐረግ አራተኛ ትውልድ ናቸው። በበአላቸው ቀን ጥቅምት ፲፬ መጥቶ ቦታውን የተሳለመ የረገጠ እስከ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ ቦታህን ጽርሐአርያም ብዬ ሰይሜዋለሁ እንደ ደብረ ታቦር ይሁንልህ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጥቷአዋል።

፫ኛ አቡነ መዝገበ ስላሴ

የሚገኙበት ቦታ ከዓዲግራት ከተማ በስተምስራቅ ጉንዳጉንዶ ማርያም ከምትገኝበት ነው በእጅህ የመነኮሰ ከቦታህ መጥቶ የተሳለመ በቃልኪዳንህ ጸንተው በጸሎትህ ለሚተማመኑት ዝክርህን ላደረጉ ፹ እልፍ ከ፮፪ ትውልድ እምርልሃለሁ ያረፈበት ቀን ጥቅምት ፱ እድሜአቸው ፮፪፭ አመት ነው።

፬ኛ አብርሃ አጽብሃ (ነገስተ አክሱም)

ትውልድ ሀገራቸው ኢየሩሳልም የእናታቸው ስም ሶፊያ ትባላለች አብርሃ አጽብሃ

የተሰወሩት መጋቢት ፳፱ ቀን አብረሀ በጥቅምት ፭ ቀን ፫፻፱ ዓ.ም በሰማዕትነት አርፈዋል አጽብሃ ደግሞ ፲፫ ዓመት ቆይተው ጥቅምት ፬ ቀን አርፈዋል። ከአብርሃ፡

አጽብሐ ቦታ የተቀበረ ጎለጎታ እንደተቀበረ ይቆጠርለታል። ከቦታው ሐዶ የተሳለመ እስከ ፲፭ ትውልድ ቃል ኪዳን ተቀብለዋል። ለመምጣት አስቦ በህመም ምክንያት የቀረ እስከ ፬ ትውልድ እምርልሀለሁ ለተራበ ያበላ ለተጠማ ያጠጣ ላጣ ያበደረ እስከ ፫ ትውልድ እምርላችኃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። የሚገኙበት ቦታ ውቅሮ መርድ ከተማ።

፭ኛ አቡነ ገሪማ

የሚገኡበት ቦታ አድዋ ቦታህን መጥቶ የረገጠ እስከ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ ብሎ ጌታ ቃል ገብቶላቸዋል። የተሰወሩበት ቀን ህዳር ፳፭ ቀን ነው የሚገኙበት ቦታ ከአደዋ ወጣ ብሎ እዳጋ አርብ ከተማ ነው።

፮ኛ አቡነ ጽሕማ

የሚገኙበት ቦታ ከአድዋ ወጣ ብሎ እዳጋ አርብ ከተማ ነው የእረፍታቸው ቀን ጥር ፲፭ ቀን በእረፍትህ ቀን ስምህን የጠራ ዝክርህን ያዘከረ እስከ ፲፱ ትውልድ ምሬልሀለሁ ካህንም ቢሆን ክህነቱ ቢፈርስበት ድንግልም ቢሆን ሐመረ ድንግልናው ቢፈርስበት የድንግልና ክንፍ አበቅልለታለሁ። ቤተ ክርስቲያንህን የሰራ ካህንም ዲያቆንም ሆኖ ያገለገለ እስከ ፲፪ ትውልድ እምርለሀለሁ። በዕለተ እረፍትህ በፍልሰትህ ቀን ከቤተክርስቲያንህ የቆረበ እስከ ፲፪ ትውልድ እምርልሀለሁ። ገድለ መጽሐፍህን የጻፈ ያጻፈ ፲፱ ትውልድ እምርልሀለሁ። ስምህን የጠራ ዝክርህን ያዘከረ ፲፭ ትውልድ እምርልሀለሁ። ገብረ ጽሕማ ወለተ ጽሕማ ብሎ ልጁን የሰየመ ፲፭ ትውልድ ምሬልሀለሁ። ቤተ ክርስቲያንህ በተሠራበት ቦታ የተቀመጠ ፲፭ ትውልድ ምሬልሀለሁ። በእረፍትህ ቀን እጣን ዘቢብ ያመጣ ፲፪ ትውልድ ምሬልሀለሁ ድውያንን። የጠየቀ ያዘነውን ያረጋጋ የታሰረውን ያስፈታ እስከ ፭ ትውልድ ምሬልሀለሁ ከዚች ቤተ ክርስቲያን የተቀበረ ፲፬ ትውልድ ምሬልሀለሁ ንጉስ ቢሆን ጳጳስ ቢሆን አምላክ ጽሕማ ብሎ ቢማጸን ፹ ትውልድ እምርልሀለሁ። ጳጳሳት ካህናት ዲያቆናት መነኮሳት ሀመረ ድንግልናቸውን ቢሰናከሉ አምላክ ጽሕማ ብለው ቢለምኑ በአንተ ጸሎት እምራቸዋለሁኝ።

፯ኛ አቡነ ጉባ (አባ ጉባ)

የሚኖሩበት ቦታ ከአደዋ በስተምስራቅ በኩል የተሰወሩበት ቀን ሰንበት ፳፱ በዚህ በተሰወሩበት ቦታ መጥቶ በዓልህን ያከበረ አስከ ፲፱ ትውልድ ምሬልሃለሁ ለቤተክርቲያንህ አጣን ዘቢብ የሰጠ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ በበዓልህ ቀን አንተ በምትጠራበት ቤተክርስቲያን ሥጋውን ደሙን የተቀበለ ፲፯ ትውልድ እምርልሃለሁ።

፮ኛ አቡነ ጴንጤሌዎን

የሚገኙበት ቦታ አክምሱም ከተማ ከቦታህ መጥቶ የዕለት ውዳሴ ማርያም የደገመ የጸለየ የተማጸነ ከልጅነት እስከ እውቀት የሰራውን ሀጢአት አስተሰርይለታለሁ። ለቤተ ክርስቲያንህ አጣን ጧፍ ዘይት ስንዴ የሰጠ አሰከ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ አንተም የኢትዮጵያን ህዝብ ማርልኝ ብለህ ስለለመንከኝ እነሱም በአንተ ጸሎት ቢያምኑ ምሬልሃለሁ የተሰወሩበት ቀን ጥቅምት ፮ ነው።

፱ኛ አቡነ ሰላማ

የሚገኙበት ቦታ ተንቤን ውስጥ ወርቅ አምባ ከምትባል ስፍራ ነው። አስቦ መጥቶ ቤተክርስትያንህን ቢሳለም ፵ ትውልድ እምርልሃለሁ አልፎ ሲሔድ ቢሳለም ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ መጽሐፍ ገድልህን ቆሞ የሰማ የቸ አመት ሀጢአቱን እፍቅለታለሁ ተቀምጦ ለሰማ የ፵ ዓመት ሀጢአቱን እፍቅለታለሁ የአባታቸው ስም ፍሬምናጦስ የእናታቸው ስም ማርያም ሰናይ ይባላል። ከአመቤታችን በቀር የሚበልጥህ የለም ተብለዋል ዝክርህን የዘከረ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ እጣን ዘቢብ ያመጣ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ በበዓልህ ቀን ፍርፋሪ የቀመሰ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ ለክብረ በዓልህ እንጨት የለቀመ ሳር ያጨደ መጽሃፍህን የጻፈ ያጻፈ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ። መጋቢት ፳፯ በእረፍትህ ቀን የመጣ ኢየሩስሌም እንደሔደ እቆጥርለታለሁ እንደገናም ፯፱ ግመል ጭነት ትውልድ እሰጠዋለሁ ያረፈበት ቦታ ሰሰሜህራቅ ትባላለች። ወለተ ሰላማ ገብረ ሰላማ ተብሎ የተሰየመ ፲፭ ትውልድ እምርልሀለሁ።

፲ኛ አቡነ ሊቃኖስ

የሚገኙበት ቦታ አክሱም ፅዮን የሚከብሩት ህዳር ፳፭ በእረፍትህ ቀን በተሰወርህበት ቀን መጥቶ የተሳለመ እስከ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ።

፲፩ኛ አቡነ ዮሐኒ

የሚገኙበት ቦታ ተንቤን በአብየአጲ ከተማ ነው ሐናጻው እንደ ላሊበላ ነው የሚከብሩበት ቀን ጥቅምት ፭ ስምህን የጠራ ዝክርህን ያዘከረ ቤተ ክርስቲያንህን የተሳለመ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ ማጅራት መቺ ቢሆን ዘማዊ ቢሆን ነፍሰ ገዳይ ቢሆን መጥቶ ቤተክርስቲያንህን ቢሳለም ያለፉ ሐጢአቱን ይቅር እለዋለሁ።

፲፪ኛ አቡነ ዳንኤል

የሚገኝበት ቦታ ደብረ ግስ ከድንጋይ የተቀረጸ ቤተክርስቲያን ከዚህ ቤተክርስቲያን መጥቶ የተሳለመ ኢየሩስአሌም እንደተሳለመ ይቆጠርለታል። እንደ ደብረ ሊባኖስ፡ ዝቋላ ቤተ ልሔም፡ አክሱም ፅዮን፡ ዋልድባ እንደተሳለመ ይቆጠርለታል። ስምህን የጠራ ፲ ትውልድ እምርልሃለሁ። በስምህ የተሰየመ ፮ ትውልድ እምርልሃለሁ። አምላክ ዳንኤል ብሎ የተማጸነ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ መጽሐፍን የጻፈ ያጻፈ ፲፱ ትውልድ እምርልሃለሁ። በፍልሰትህ ቀን ለተራበ ያበላ፤ ያጠጣ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ። በእለተቀንህ የተጠመቀ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ። ሚያዝያ ፲ በፍልሰትህ ቀን የተሳለመ ኢየሩስአሌም እንደተሳለመ እቆጥርለታለሁ ፲፯ ትውልድ እምርልሃለሁ።

፲፫ኛ ቅድስት አርሴማ

የምትገኝበት ቦታ ከወልድያ ዝቅ ብሎ መርጦ ኢየሱስ ከሚባል ቦታ ነው። የምትከብርበት ቀን መስከረም ፳፱ እና ታህሳስ ፮ ቀን ነው። በተሰየፍሽበት ቀን መጥቶ ቤተክርስቲያን የተሳለመ ፲፪ ትውልድ እምርልሻለሁ። መጽሀፍ ገድልሽን የሰማ ያሳማ ፲፪ ትውልድ እምርልሻለሁ። ከቤተ ክርስቲያንሽ መጥቶ የፀለየ የለመነ የልቡን ፍላጎት እፈጽምለታለሁ። እኔ በህይወት መጽሐፍ ስሙን ያልጻፍኩት ቦታሽን አይረግጥም ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላታል።

፲፬ኛ አቡነ ፍሬ ካህን

የሚገኙበት ቦታ ከእንዳባጉና በስተምእራብ ነው። የአቡነ ቶማስ ልጅ ናቸው። የሚከበሩበት ቀን ህዳር ፫ በእረፍትህ ቀን መጥቶ የተሳለመ ፳ ትውልድ እምርልሃለሁ አምላክ ፍሬ ካህን ብሎ የተማጸነ ለዝክርህ እንጨት የለቀመ የጉዝጓዝ ሳር ያጨደ ፳ ትውልድ እምርልሃለሁ።

፲፭ኛ ማህበረ ዶጌ /ማህበረ ጻድቃን

የሚገኙበት ቦታ ከአክሱም ከተማ ወጣ ብሎ አክሱም የገቡበት ጊዜ ፫፻፴፯ ዓ.ም ፱፫፱፱ ጻዱቃኖች መጥተው የገቡበት ነው። የተሰወሩት ጥር ፴ በስማቸው የዘከረ ቦታውን የረገጠ ፲፬ ትውልድ እምርላቸዋለሁ። በተሰወሩችሁበት ጥር ፴ መጥቶ ቤተክርስቲያናችሁን የተሳለመ ዝክራችሁን ያዘከረ በዕለተቀናችሁ ፍርፋሪያችሁን የቀመሰ ቤተክርስቲያን ያሳነጸ ለተራበ ያበላ ለተጠማ ያጠጣ ፲፬ ትውልድ እምርላችዋለሁ። ለታረዘ ያለበሰ እኔ የሕይወት ልብስ አለብሰዋለሁ።

፲፮ኛ አፄ ይኩኖ አምላክ

ለገነተ ማርያም የተሰጣቸው ቃል ኪዳን እንደ ዳዊት ያለ ክብር ሰጥቼሃለሁ። ከቦታህ መጥቶ የጸለየ መንግስተ ሰማያት አገባዋለሁ። ከዚህ ቦታ የተሳለመ ዘውገ መላእክት ይባላል። ገነተ ማርያምን ለማየት የተመኘ የፈለገውን ብዙ እድሜ ሰጥቼ መጥቶ ቦታህን እንዲረግጥ አደርገዋለሁ። ተመኝቶ ቢቀር በነፍሱ መንግስተ ሰማያት እንዲገባ አደርገዋለሁ ለገነተ ማርያም ጥላ ያስገባ ሁሉ መንግስተ ሰማያት ይገባል ብዬ ቃል ኪዳን ገብቼልሃለሁ። አምላከ ይኩኖ አፄ ይኩኖ አምላክ ብሎ ባለበት ቢያስታውሰኝ በእንተ ፀሎት እምረዋለሁ ጠቅላላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ እናቴ እንደ ማርያም አስራት አድርጌ ሰጥቼዋለሁ እስከ የተጻደለው ፀሎቱ ሁሉ ዛሬ ድረስ የጸለየው ጸሎቱ ሁሉ በዚህ እለት ታህሣሥ ፭፭ ቀን ተሟልቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ለእናቴ ለማርያም ቃል ኪዳን ሰጥቻለሁ። ገነተ ማርያም ድረስ ሔዶ ስጋና ደሙን የተቀበለ አቡነ ዘበሰማያት የደገመ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ። የአባታቸው ስም አቡነ ጽዮን ሀገራቸው ሸዋ ቡልጋ መናፍቃን መጥተው ቦታህን ቢሳለሙ አልምርልህም ተብለዋል። ቦታህ ብርሃነ መለኮቱ እንደገለጽህበት እንደ ደብረ ታቦር ትሁንልህ። ከዚህ ቦታ መጥቶ የተሳለመ የሰንበት ያህል ክብር አለው ገነተ ማርያም ምድራዊ ገነት ስትሆን ሰማያዊ ገነት ብያታለሁ።

፲፯ኛ ናአኩቶ ለአብ

የሚገኙበት ቦታ በሰሜን ወሎ ነው የቅዱስ ላሊበላ የታላቅ ወንድሙ ልጅ ነው። የአባቱም ስም ገብረ ማርያም ነው። ከመወለዳቸው በፊት በእናታቸው ማህጸን ሁነው ፱፱፱ እልፍ ነፍሳት አውጥተዋል። ከተወለዱ በኋላ ግን ፭ ፴ ፱ ፭ ፭ ፯ በየጊዜው ሲያወጡ ኑረዋል። እንደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እህል አልበሉም መጠጥም አልጠጡም። ሰንበት እንዳይሽር ቅዳሜና እሁድ አፈር ይቀምሱ ነበር ከሩቅና ከቅርብ መጥተው የተማጸኑ የአንድ አመት ነጠብጣብ ዝናም ብዛት ያህል ምርልሃለሁ። በቀኝና በግራ ትከሻው በቅዱስ ገብርኤል ማሕተም ታትሞ በዕለተ ምጽአት ጊዜ የአንተ ምርኮኛ ይሁንልህ መለያቸው ይሕ ማህተም ይሁንልህ ከቦታህ መጥቶ ሓጢአት አለብኝ ብሎ የተጠራጠረ እንደ ይሁዳ ይሁን የተሰወረበት ቦታ አሸተን ማርያም ልዩ ስሟ ደብረ ጽዮን የተሰወረበት ቀን ህዳር ፫ ነው።

፲፰ኛ ላሊበላ

የሚገኘው በላስታ ከተማ ውስጥ ነው። በነገሰ ፫፻፹፭ ዓ.ም በነገሰ በ፲ አመቱ ቤተ

ክርስቲያን መስራት ጀመረ። ፫፻፹፭ ዓ.ም ቤተማርያምን ስራ መስከረም ፭፻ ፈጸመ። ቀደሰ ነሓሴ ፲፫ መደኃኒዓለምንም ፈጸመ ቀደሱ ታህሳስ ፭፭ አማኑኤልን ፈጸመ ቀደስ ህዳር ፮ ጊዮርጊስን ፈጸመ ቀደስ ሚያዝያ ፴ ቤተ ጎለጎታን ፈጸመ ቀደስ ታሕሣሥ ፲፱ ገብርኤልን ፈጸመ ቀደስ ጥር ፫ ቤተ ላሊበላን ፈጸመ ቀደስ ነሐሴ ፮ ቤተ ደናግልን ፈጸመ ቀደስ ህዳር ፭፭ ቤተ መርቆሬዎስን ፈጸመ ቀደስ ምስቀል ክብራ ፈጸመ ቀደሰ ። ተፈጸመ በእግዚአብሔር ቸርነት አሜን።

፲፱ኛ ገብረ ክርስቶስ

የትውልድ ሀገሩ ቁስጥንጥንያ ትባላለች። የናቱ ስም መርኬዛ አባቱ ቴዎዶስዮስ ይባላል። የእረፍት ቀን ጥቅምት ፲፬ ነው። በጸሎትህ የተማመነውን ገድልህን የጻፈውን ያጻፈውን በመታመን ዜናህን የሰማውን ለመታሰቢያህ ስንዴ ወይን እጣን ያመጣውን ለዝክርህ እንጨት ውሃ ሳር ያቀረበውን ዝክርህን ያዘከረውን ፍርፋሪህን የቀመሰውን ለቅዱሳን በሚዘጋጀው በምስህ ደብረ ፅዮን እንዲገኙ አደርግልሀለሁ በመታሰቢያህ ቀን ፀሎትህን ተስፋ አድርገው በመአልትም በሌሊትም ቢሆን በቤተክርስቲያንም ሆነ በሌላ ቦታ ዜናህን ሰምተው እንባቸውን ቢያፈሱ ቸርነቴን አደርግላቸዋለሁ። ዝክርህ በተደረገበት ገድልህ በተነበበት ይቅርታ ቸርነት ለዘለዓለም በዚያ ይሁን ገብረ ክርስቶስ በስደት ፲፭ ዓመት ከዚያ ተመልሶ በቤተሰቡ ቤት ተመጽዋች ሆኖ ስያውቁት ፲፭ ዓመት በአጠቃላይ እድሜው ፵፭ ዓመት ሲሆነው ጥቅምት ፲፬ አረፈ።

፳ኛ ክርስቶስ ሳምራ

የትውልድ አገሯ በቡልጋ አውራጃ ቅዱስ ጌ የተባለች አገር ናት። የአባቷ ስም ደረሳኒ የእናቷ ስም እሌኒ ይባላል። ያረፈችበት ቦታ ጣና ሐይቅ ኋንጉት የሚባል ሲሆን

ያረፈችውም ነሐሴ ፳፬ ነው። ጌታ ቃል ኪዳን ሲሰጣት መታሰቢያሽን ያደረገ ስምሽን የጠራ በቤተ ክረስቲያንሽ የተቀበረ እስከ ፯ ትውልድ እምርልሻለሁ። ይህች ደሴት እንደ ደብረ ታቦር እና ደብረ ዘይት ስሟ የተጠራ ይሁን ስሟም ደብረ ፍቅር ደብረ ምህረት ተብሎ ይጠራ አላት። ስጋሽ ከተቀበረበት መካነ መቃብርሽን የተሳለመ የእናቴን የማርያምን መካነ መቃብር እንደተሳለመ ይቆጠርለታል።

፳፭ኛ አቡነሐበተ ማርያም

የትውልድ ቦታቸው በመንዝ ክፍለ ሀገር የራዊ ከምትባል ስፍራ ነው። ነሐሴ ፳፯ ቀን ተጸነሱ፤ ግንቦት ፳፯ ቀን ተወለዱ፤ ሕዳር ፳፯ ቀን አረፉ። እናታቸው ቅድስት ዮስቴና አባታቸው ዘርዓብሩክ ይባላሉ። አቡነ ሀብተማርያምን ጌታችን ፷ቱን ማዕዘናት በመስቀላቸው እንዲባርኩ አዘዛቸው። ሲባርኩ ፫ አጋንንት በማየታቸው ደነገጡ ጌታም አጸናቸውና ሰውን እንዴት እንደሚያስቱ ጠይቃቸው አላቸው። እሳቸውም ጠየቁቸው ከጠየቁቸውም በኋላ እኔንስ እንዴት ታስቱኛላችሁ ቢላቸው እንኳን አንተን ልናሰትህ በአንተ ጸሎት የተማጸኑትን ማሳት አይቻለንም ብለዋቸዋል። ከዚህ በኋላ የቆምክበትን ምድር ባርክ አላቸው ጌታ፤ ሲባርኩ ምድር አፏን ከፍታ ሁለቱን ሰይጣናት ዋጠቻቸው። እንደኛው ግን ስለ ህያው እግዚአብሔር ብለህ አታጥፋኝ ብሎ ሲለምን መድኃኒዓለም ይህንስ ተወው ጊዜው አልደረሰም አላቸው። ለቀቀው እና ሄደ። ጌታም ቃል ሲገባላቸው በአንተ ጸሎት የተማመነውን ስምህን የጠራውን ዝክርህን የዘከረውን ገድልህን የሰማ ያሰማውን ከአምስቱ መቅሰፍቶች እጠበቃቸዋለሁ እነሱም፡ መብረቅ፤ እሳት፤ ንዳድ(ወባ)፤ ተቅማጥ እና ወረርሽኝ(ተስቦ) ከእነዚህ በሽታዎች እታደገዋለሁ። ስለእነዚህ አምስቱ መቅሰፍቶች ሲል ወዳጄ ተክለሃይማኖት በእርሱ ቦታ እንድትቀበር ለምኖኛል እና ቀብርህ በደብረ ሊባኖስ ይሁን ብሎአቸው ከዚያው ተቀብረዋል።

፳፮ኛ አባ ኪሮስ

የመጀመሪያ ስማቸው ዲላሶር ይባላል። በአባታቸው ሮማዊ በእናታው ሶርያዊ ሲሆኑ የነግስታት ዘር ናቸው። አባትና እናታቸው በአንድ ግዜ መንታ ልጅ ተወለዱላቸው የመጀመሪያወን ቴዎዶስዮስ ሁለተኛውን ዲላሶር ብለው ሰየሚቸው ጊዜ ሞታቸው ሲደርስ ሀብታቸውን ሁለት እኩል እንዲካፈሉ ተናዘውላቸው ሞቱ። ቴዎዶስዮስ በአባቱ ምትክ ነግሶ ሲኖር ዲላሶር አባ ኪሮስ የወላጆቻቸውን ሀብት እንዲያካፍላቸው ወንድማቸውን ቢጠይቁት ፍቃደኛ አለመሆኑን አይተው ለዚህ ዓለም አላፊ ጠፊ ሀብት መጨቃጨቅን ጠልተው የማያልፈውን ሀብት ፍለጋ አገራቸውን ለቀው በምናኔ ወደ ግብፅ ሀገር ሔደዋል።በዚያም በአንድ ተራራ ላይ እድሉ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ኪሮስ በማለት ጠርቶ አባብኑዳ ወደሚባል መነኩሴ እንዲሄድ አመልክቶቸው ከሚኖሩበት ዋሻ ሔደው አመነኮሱአቸው የብሉይ እና ሀዲስ ትርጓሜ አስተምረው ቅስና ቁምስና አስመጥተው አርአያቸውን እየተከተሉ ዘውትር በሰረክ በመላእክት እጅ የሚላክላቸውን ሰማያዊ ሁበስትና ፅዋዕ አብረው እየተመገቡ በጸሎትና በስግደት እግዚአብሔርን እያገለገሉ ለብዙ ዘመናት ኖረዋል። ከእለታት አንድ ቀን አንድ መነኩሴ የገዳም ልብስ ለብሶ በእንግድነት ወደ በዓታቸው መጣ። አባ ብኑዳም ከየት እንደ መጣ ጠይቆ አሳደረው። ይህም እንግዳ መነኩሴ በዋሻው የምግብ ማብሰያ እቃና ጥራጥሬ ባለማየቱ እንዴት እንደሚመገቡ ቢጠይቃቸው እግዙአብሔር እንዳሰኝ-------- አለው። የሰርክ ጸሎት በአንድነት አድርሰው እንደጨረሱ መልአኩ እንደተለመደው ሕብስተ መና ጽዋዕ ሕይወት አምጥቶላቸው ሲመገቡ ያ እንግዳ መነኩሴ በምትሃት እንዳስገኙት በመቁጠር ከምግቡ ቆርሶ በመጠምጠሚያው በመደበቅ ወደ መጣበት ገዳም ሄዶ የገዳሙን መነኮሳት በደውል ሰብስቦ የአባብኑዳን መሠረነት ገልፆ ደብቆ ያመጣውን ሕብስት ሲያሳያቸው መላኩ ወርዶ በክንፍ አጣፍቶ መናውን ቀምቶ አርጓል። ከዚያም የተቀደሰውን ሰማያዊ ሕብስት ለማይገባው ውሻ በመስጠታቸው መናው ተቋረጦባቸው አባ ኪሮስ ምግባቸውን ወደ ጫካና ገደላገደል እየሔዱ ፍራፍሬ እና ስራስር እየለቀሙ የሚመገቡ ሆነዋል። አንድ ቀን እንደልማዳቸው ምግብ ፍለጋ ሔደው ሲመለሱ አባብኑዳን አንበሳ በልቶት የተራረፈውን ሥጋ ተበታትኖ አገኙት። አባ ኪሮስ ይህን በማየታቸው ምርር ብለው አልቅሰው የተበታተነውን ሥጋ ለቅመው በዋሻው ውስጥ አስቀምጠው ወደ ፈጣሪያአቸው እያለቀሱ ከአንተ እውነትና ፍርድ እስካገኝ ድረስ እንዳልነሳ በሕያው ስምህ እምላለሁ ብለው በግንባራቸው ተደፍተው ከመሬት ላይ ተኙ በዚያም ምስጥ መጣባቸው ጉንዳን ወረራቸው ዝናብ ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው ፵ ቀን ሙሉ ሣር እስከሚበቅልባቸው ቆይተዋል። ከዚህ በኋላ ጌታ ተገልፆ መከራህን አይቻለሁ ጸሎትህንም ሰምቻለሁ አባትህ አባ ቡብኑዳ የታዘዘውን ረስቶ የተቀደሰውን ለውሻ በመስጠቱ ይህ ሁሉ መከራ ደረሰባችሁ። አሁንም ወዳጄ ሆይ ተነስ በቃህ ብሎ አስነስቷቸዋል። ከዚህ በኋላ የሀጥአንና የጻድቃን ነፍስ ከስጋቸው ተለይታ የት እንደምትገባ ተገልጾላቸው ገነትን እየዞሩ አይተዋል። አባብኑዳም ከብዙ ነፍስ መካከል የብርሀን አክሊል ደፍተው የብረሀን ልብስ ለብሰው በወርቅና በእንቁ በጌጠ ወንበር ተቀምጠው አይተዋል። ወደ ዋሻቸውም ተመልሰው በጾም በጸሎትና በስግደት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሲኖር አንድ ቀን ሰይጣን ሰው መስሎ መጥቶ አሳድሩኝ አላቸው። እርሳቸውም ከየት እንደመጣ ቢጠይቁት የመጣሁበት ምን ያደርግልሀል አሳዱረኝ አልኩህ እንጂ ብሎ

በትዕቢት ስለ መለሰላቸው ሰይጣን መሆኑን አውቀው ከዋሻው ውስጥ ራቅ ባለ አንድ ክፍል ውስጥ አስቀመጠው ቢፀልዩበት ከዋሻው እንዳይወጣ ዝግ ሆኖበት እየጮኸ ኪሮስ ሆይ ሳልቀድምህ ቀደምከኝ እስከ መቼ ነው በዚህ ተዘግቶብኝ እምኖረው ቢል እስከ ምጽአት ብለውት እስከአሁን በዚያው እየጮኸ ይኖራል አባኪሮስ በዋሻ ተወስነው መኖር ብቻ ሳይሆን በግብፅ ሀገር እየተዘዋወሩ ወንጌልን አስተምረዋል ብዙ አህዛብንም አሳምነዋል አጥምቀዋል። ከዚያም ወደ ዋሻቸው ተመልሰው እንደቀድሞው ሕብስት ሰማያዊ እየወረደላቸው በጸሎት ተወስነው ኖረዋል። እግዚአብሔርም ብርታታቸውንና ቅድስናቸውን አይቶ ወዳጄ ኪሮስ ሆይ ስምህን የጠራ መታሰቢያህን ያደረገ ገድልህን የፃፈ እና ያፃፈ ያነበበ እና የተረጎመ በስምህ የተራበ ያበላ የተጠማ ያጠጣ የታረዘ ያለበሰ ለቤተ ክርስቲያህን መበአ የሰጠ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ብሎ ቃል ኪዳን ሰጥቶአቸዋል። ጊዜ እረፍታቸው ሲደርስ አባ ዓውማ የተባለ መነኩሴ ታዘላቸው ታሪካቸውን እየጠየቀ እግዚአብሔር ያመለከተውን እየጨመረ ገድላቸውን ጽፎአል። ከዚህም በኋላ ሥጋው ደሙን ተቀብለው በ፪፻፷ አመታቸው ሐምሌ ፳ ቀን አርፈዋል። አባ ባውማም ከገነዟቸው በኋላ መላእክት መጥተው የነበሩበትን ዋሻ ዘግተው አስከሬናቸውን በደብር ቅዱስ አስቀምጠዋቸዋል።

፵፫ኛ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ

የትውልድ ሀገሩ ኢየሩሳሌም ሲሆን የተወለደውም ብዙ እልፍ ሕፃናትን የፈጀ ሔሮድስ ነግሶ በነበረበት ወቅት ነው። አባቱ ዘካርያስ እናቱ ኤልሳቤጥ ናት። የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘመዷ ነች ሄሮድስ ኢየሱስን ለማግኘት እና ለመግደል በፈለገ ጊዜ ሕጻናትን ሲያስፈጅ ኤልሳቤጥ ልጇን ይዛ ወደ በረሀ ሸሽች። በዚያም እየኖሩ ሳለ ዮሐንስ ፭ ዓመት ሲሞላው እናቱ ሞተችበት። ይህንንም ጌታ ተረድቶ በናዝሬት ሳሉ ሲያለቅስ እመቤታችን ጠየቀችው እና ስለ ኤልሳቤጥ ሞት ነግሯት ሰሎሜን አስከትለው ወደበረሃ በመሄድ ቅዱስ ሚካኤል እና ቅዱስ ገብርኤል ቀብረዋታል። ጌታም እኔ በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ በማመስገኗ እንኳን ስጋዋ ሊፈርስ ይቅርና መግነዟም አይለወጥም መቃብሯም አይጠፋም ነፍሷም ከስጋዋ እንዳትለይ አደርጋለሁ ብሎ ለወዳጁ ለዮሐንስ ገልፆለት በበረሀ ትተው ሄደዋል። ዮሐንስም ፴ አመት በሞላው ጊዜ ሄሮድስ ህግን አፍርሶ የወንድሙን ሚስት ቀምቶ አገባ በዚህም ጊዜ ዮሐንስ በቅዱስ ገብርኤል አምሳል ሌሊት ተኝተው ሳለ ይዘልፋቸው ነበር። ነገር ግን ድምጹን ይሰማሉ እንጂ አያዩትም። ሄሮድያዳም ለንጉሱ ይህ ድምፅ የዛ የአስማተኛ የዮሐንስ ድምፅ ነው ደብረ ሲና በረሀ ወታደሮች ልከህ ማንም ሳይሰማ አስገድለው አላቸው። ወታደሮቹ ግን ሊያገኙት አልቻሉም። ጌታ ፴ አመት ሲሞላው መንፈቅ በቀረው ጊዜ ዮሐንስ ፴ አመት ሲሞላው መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ማስተማር ጀመረ ሕዝቡንም ሀጢአታቸውን እያናዘዘ በዮርዳኖስ ውሀ ያጠምቃቸው ነበር። ሄሮድያዳም ዮሐንስን በግልጽ ማስተማር በሰማች ጊዜ እጅግ ደስ አላትና ጠላታችን በግልፅ ተገኘ ከእንግዲህ ወዲህ አይናገረንም ብላ ነገረችው እሱም ከእንቺ አብልጬ የምወደው የለም ታዲያ ይህ ነብይ ይዘልፈናል አላት እርሷም በዚህ ነገር አትዘን የልደትህን በአል ከምታከብርበት ቀን በፊት ዮሐንስ እንዲታሰር አድርግ ከዚያም ከመኳንንቶች ፊት ልጇ ትዘፍንልሃለች የዮሐንስን አንገት ቆርጠህ ስጣት አለችው። በዚህም እድል ከአንድም ፪ ጊዜ ዮሐንስ ደቀመዛሙርቶቹን ልኮ ዘለፈው። እሷም ምክንያት ለማስመሰል እንዲመችህ ባሌን ፊልጶስ ግደለው ከዚያም እርሱ ስለሞተ አግብኒት ትላለህ አለችው። እንዳለችውም አደረገ። ዮሐንስም ከዚህ በኋላ በሕዝቡ መሐከል በግልፅ የወንድምህን ሚስት ማግባት አትችልም እያለ ይዘልፈው ጀመር በዚህም ምክንያት አድርጎት አስረው የሄሮድስም ልደት በደረሰ ጊዜ ማለትም የዘመን መለወጫ በአል መስከረም ፪ በልደቱ ላይ የሄሮድያዳን ልጅ ጌጠኛ ልብስ ለብሳ ዘፈነችለት። እርሱም ደስ በመሰኘቱ የፈለግሺውን ለምኚኝ የመንግስቴን እኩሌታም ቢሆን እሰጥሻለሁ ብሎ በመኳንንቶች ፊት ቃል ገባላት። እርሷም ደስ በማለቱ የፈለግሽውን ለምኚኝ የመንግስቴን እኩሌታም ቢሆን እሰጥሻለሁ ብሎ በመኳንንቶች ፊት ቃል ገባላት። እርሷም እናቷ እንደመከረቻት የዮሐንስን አንገት ቆረጠህ ስጠኝ አለችው። ንጉሱም ቅር ተሰኝ አዘነ እንቢ እንዳይል ከዳ መሃላውን አፈረሰ ሊባል ነው አስቆርጦ እንዳይሰጣት ጌታን ያጠመቀ ሕዝቡም በጣም የሚያመልከው ነቢይ ነው ነገር ግን ሰራዊቱን አዞ የዮሐንስን አንገት ከወሐኒ ቤት በወጭት እንዲልኩላት አድርጎ ለሄሮድያዳ ልጅ ሰጣት። የዮሐንስን አንገት ግን በሳህን ላይ ሆኖ ሔሮድስ የወንድምህን ሚስት ማግባት አይገባህም እያለች በመኳንንቱ ፊት ዘለፈችው። ልጅቷም ወስዳ ለእናቷ ሰጠቻት። በወህኒ ቤት የወደቀውን በድኑን ዮና የምትባል የንጉሱ እቃ ቤትጠባቂ ደቀ መዛሙርቱ እስከሚወስዱት ድረስ በክብር ቦታ አስቀመጠችው። እነሱም ሌሊት ወስደው በነቢዩ በኤልሳ መቃብር ቀበሩት። ሄሮድያዳም የልቧ ስለደረሰላት የዮሐንስን አንገት በጥፊ ለመምታት እጇን በዘረጋች ጊዜ ክንፍ አውጥታ እንደ ንስር በራ ሄደች። ያን ጊዜ የሄሮድያዳ እጆች ከትከሻዋ እየተቆረጡ ወደቁ ሰውነቷም መሬት ተከፍታ እስከ አንገቷ ዋጠቻት ከዚያም የዮሐንስ አንገት ፲፭ አመት እየዞረች ስትስተምር ኑራ ሚያዚያ ፲፭ ቀን አረፈች።

ደቀመዝሙርቱም በኤልሳ መቃብር ቀበሯት ጌታም ቃል ሲገባለት ስምህን የጠሩ መታሰቢያህን የሚያደርጉ ወደ ስጋዊ ተግባርም ሲሔዱ ቢሆን ቤተክርስቲያንህ ገረገራውን ቢሳለሙ እስከ ፱፭ ትውልድ እምርልህለሁ በስምህ የዘከሩ ለተቸገረ በስምህ ያበደሩ እስከ ፲ ትውልድ እምርልህለሁ። ከቤተክርስቲያንህ የተቀበረ ወደ ቤተክርስቲያንህ ከሩቅም ከቅርብም የሄደ እስከ ፱፭ ትውልድ እምርልህለሁ። ወደ ቤተክርስቲያንህ ለመሄድ አስቦ በሕመም፡ በእርጅና ቢቀር መንገድ ጀምሮ ቢመለስ እንደ ተሳለመ እቆጥርለታለሁ እስከ ፲፪ ትውልድ እምርልሃለሁ። መስከረም ፭፤ ሚያዝያ ፲፭ እና ሰኔ ፴ በማህሌት በእጁ እያጨበጨበ እያሸበሸበ ያከበረ እስከ ፱፭ ትውልድ እምርልህለሁ። በስምህ የታመመ የጠየቀ ያዘነ ያረጋጋ እስከ ፯ ትውልድ እምርልህለሁ ገድልህን የፃፈ ያፃፈ ያነበበ እና የተረጎመ ተነቦ ሲያበቃ ገበታውን የሳመ ሲነበብ የሰማ እስከ ፱፭ ትውልድ እምርልህለሁ የገድልህ መጽሐፍ በተነበበት ውህ የተጠመቀ ሰው ቢኖር እስከ ፹ አመት የሰራውን ኃጢአቱን አስተሰርይለታለሁ ወንዱን የሟ ቀን ሴቷን የ፹ ቀን ሕጻን አደርጋቸዋለሁ። እኔ በተጠመቅሁበት ማየ ርዳኖስ እንደተጠመቀ ይሆናል። ለታረዘ ያለበሰ ገድልህ የተነበበትን ማየ ጸሎት ከቤቱ የረጨ እስከ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ።በስምህ እንግዳ የተቀበለ እስከ ፲ ትውልድ እምርልሃለሁ። ደስ ብሎት በዓልህን ያከበረ ለቤተክርስቲያንህ እጣን፤ ሻማ፤ ልብሰ ተክህኖ፤ መሳናጸፊያ፤መጋረጃ፤ ነጭ ስንዴ የሰጠ ለጉዝጓዝ የሚሆን ሣር ያመጣ እስከ ፱፭ ትውልድ እምርልህለሁ መታሰቢያህን የሚያደርግ ልጅ ባይኖረው መካን ቢሆን የ ፱፭ ትውልድ ክብር ደርቤ እሰጠዋለሁ ወደ ኃላ ትውልዱን ቆጥሬ ዘሩን አድንለታለሁ።

፭፭ኛ ቅዱስ መርቆሪዎስ

የሊቀ ሰማእታት ቅዱስ መርቆሪዎስ በአለ አረፍቱ ህዳር ፭፭ ነው የተወለደው በ ፪፪፭፭ ዓ.ም ሩማንያ ውስጥ ሰካዝያ በምትባል ሀገር ሲሆን ያደገው ሮም ውስጥ ነው ዜግነቱም ሮማዊ ነበር አባቱና አያቱ አራዊትን በሚያድኑበት ጊዜ ሁለት ገጸከለባት አገኛቸው ኃሮፎሶና አርጋኔ ይባላሉ። አባቱንም ሊበሉት በወደዱ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከእርሱ መልካም ፍሬ ይገኛል እና አትንኩት ብሎ በአሳት ዙሪያቸውን ከቦ ከለከላቸው እነርሱም ስለተጨነቁ ሰገዱለት እግዚአብሔርም ያን ጊዜ ፍጥረታቸውን ወደ በጎ ለወጠ ከእርሱ ጋርም ተጠምቀው ክርስቲያን ሆኑ። ሆነው ተቀመጡ በወቅቱ ነግሶ የነበረው ንጉሥ ዳኬዎስ ባርሪያንስ የተባሉ ጠላቶች ተነሱበት በዚህ ጊዜ መርቆሪዎስ የጦር አዛዥ ነበር። የእግዚአብሔር መልአክም ተገልዖ ጦርነቱን ድል ታደርጋለህ ብሎ ሰይፍ ሰጠው በዚህም የጠላቶቹን ንጉስ ገደለ ድልም አደረገ በዚህም የሮማ መንግስት ጦር ሐይሎች የበላይ አዛዥ ሆነ ንጉስ ዳኬዎስ ድልን ያገኙልን አማልክት እነሱ ናቸው በማለት ጣዖት አቁሞ ስገድ አለው እርሱም እኔ አምላኬ እግዚአብሔር አልክድም ድልን የሰጠንም እሱ ነው ለእንተ ጣዖት አልሰግድም ብሎ ትጥቁን እና ልብሱን አውልቆ ወረወረ። በዚህም ጊዜ ሐሳቡን ይቀይራል በማለት ሕዝቡ እንዳይቃወመው ወደ ቂሳርያ ልኮ ብዙ መከራን

ተቀበለ። ከዚህም በኋላ በ ፪፪ ዓ.ም በ፭፭ ዓመቱ ህዳር ፭፭ ቀን አንገቱ በሰይፍ ተቆረጠ ጥር ፭፭ የቂሳርያ የቀጸድቂያ ሊቃነ ጳጳሳት በነበሩ በአባ ባስልዮ እና ጎርጎርዮስ ዘመን ክርስቶስን የካደ ኤልያኖስ የተባለ ከሀዲ ንጉስ ተነስቶ ክርስቲያኖችን ብዙ አሰቃየ በዚህም ጊዜ እነዚህ ጳጳሳት በሰማዕቱ መርቆሪዎስ ስም በታነፀች ቤተክርስቲያን ሕዝቡን ሰብስበው ከዚህ ከከሀዲ ንጉስ ያድናቸው ዘንድ በስዕሉ ፊት ይጸልዩ ጀመር በዚህም ጊዜ ከስዕሉ ላይ መርቆሪዎስ ከሃዲውን ንጉስ ኤልይኖስን ስለገደለው ከጦሩም ላይ ትኩስ ደም ሲንጠባጠብ ታየ ቅዱስ ባስልስም የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ቅዱስ መርቆሪዎስ ሆይ ይህን ከሀዲ ንጉስ ገደልከውን ሲል ጮኾ ጠየቀ በስዕሉ ላይ እንዳለም አዎ ለማለት እራሱን ዘንበል አድርጎ በእንቅስቃሴ አስረዳቸው ይሕንንም አብነት በማድረግ እነሆ ዛሬም በሰሜን ሸዋ አርማንያ ከተማ አጠገብ ጋሹ አምባ ቀበሌ በሚገኘው ቅዱስ መርቆሪዎስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት የስብሐተ እግዚአብሔር አገልግሎታቸውን በማህሌት በሚያደርሱበት ጊዜ በየክብረ በዓሉ ግርግዳው ላይ የሚገኘው የቅዱስ መርቆሪዎስ ስዕል በመዝለል ተአምራቱን እየገለጸ ይገኛል።

፭፭ኛ አባ እስትንፋስ ክርስቶስ

ሀገራቸው ዳውንት የሚባል ትሩፊ ምግባር የሚሆኑ የተቀደሱ አባታችን እስትንፋስ ክርስቶስ ሚያዚያ ፱ ቀን አረፉ ስሙ መልአከ ምክሩ የሚባል በደብረ አስጋጅ አንድ ቁስ ነበር ሚቱም ወለተ ማርያም ትባላለች ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚፈሩ እና እመቤታችንን የሚወዱ ነበሩ ይህን የተባረከ አባ እስትንፋስ ክርስቶስን በወለዱት ጊዜ በጣም ደስ ተሰኙ ይሕም ሕፀፃን ፫ ጊዜ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል ብሎ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ ከዚህም በኋላ ሕፃናትን ለሚያናግሩ ለዓለአዝተ አለም ሥላሴ ፱ ጊዜ ሰገዱ በዚህ ሕፃን ላይ ያደረገውን የእግዚአብሔርን ጸጋ አይተው ይሕንን ያዩ እና የሰሙ ሰዎች ፈጽመው አደነቁ የሚነጹበት ወራት በተፈጸመ ጊዜ ንጉስ ይኮኖ አምላክ ወደ አነፃት እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ወስደው መንፈስ ቅዱስ እንዳናገራቸው ስሙን እስትንፋስ ክርስቶስ ብለው ሰየሙት ከዚህ በኋላ ይኽ እስትንፋስ ክርስቶስ አደገ የስሙ ትርጓሜ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ነው ከጥቂት ቀንም በኋላ በደብረ ድባ ወደ ሚኖር አባ ኪራኮስ ፃድቅ ዘንድ አባቱ ወስደው አባቱም

አባኪራኮስን ይሕን ልጄን አስተምርልኝ ብሎ ለመነው እሱም ሕጻኑን ተቀብሎ ከተወለድሕ ስንት ዓመትሕ ነው ብሎ ጠይቆ በዚህች እለት ፊደልና ፊደለ ሐዋርያትን አስተምሮት በአንድ ቀን አወቃቸው በጥቂት ቀንም ንባብና ትርጓሜውን ጨረሰ የቤተክርስቲያንንም ትምሕርት በጨረሰ ጊዜ ስሙ ማርቆስ ወደሚባል ጳጳስ ክሕነት ይሰጠው ዘንድ አባቱ ወስደው። ጳጳሱም የሕጻኑን እውቀት ባየ ጊዜ ፈጽሞ ደስ ተሰኘ አመሰገነውም የድቁና ማዕረግም ሰጠውና ጸጋና ክብርንም ተሞላ ወደ እግዚአብሔርም ሔዶ የተልኮ ሥራ ጀመረ። በአንዲት ቀን አባቱ ለሕዝቡ ሥጋ ወደሙን ሲያቀብል በዚህች ዕለት የቆረቡት ስንት ናቸው አለው። ከሺ፬ እልፍ ሰዎች ፲፪ ሰዎች ብቻ ናቸው የቆረቡት አለው የቀሩትን ሲገርፋቸው አየ ይሕንንም አይቶ ብዙ ለቅሶ በማልቀስ ጸለየ። ታቦቱንም ተሰናብቶት ዳግመኛም አባቱንና እናቱንም ተሰናበታቸው እመነኩስ ዘንድ ወደ ገዳም እሔዳለሁ አላቸው ከዚህም በኋላ አባቱ በታቦቱ ፊት ጸለየ ያንጊዜም ከሰማይ እንዲመነኩስ ይሔድ ዘንድ አግባብ ነው የሚል ቃል ሰማ ክብሩም እስከ ሰማይ ከፍ ያለ ይሆናል። ትምህርቱ ተአምራቱ ከአዕናፍ እስከ አጽናፍ ይሰማል። ይህንን ሰምቶ ወጣ የሰማውን ሁሉ ነገረው። አቡነዘበሰማያትም ጸልዮለት በተወለደ በ፲፬ አመቱ አሰናብቶ ሸኘው ገዳማቶችን እየዞረ መልእኩም እየመራው ደብረ ሐይቅ አደረሰው። ያን ጊዜ በሙሴ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለከተ ያለ መርኩበም ባሕሩን ተሻገረ ቤተ ክርስቲያንን እጅ ነስቶ የክርስቶስ ማደሪያው ሰላምታ ይገባሻል አላት ካሕናቱ አገኙት እና ከገዳሙ ሹም ወሰዱት ገብቶም ከእግሩ ስር ሰግዶ የገዳሙ መምሕርም በመንፈስ ቅዱ አውቆ ልጄ ልትመነኩስ መጣህን አለው አዎን አባቴ አለ። የሚፈቅደውን ሁሉ አውቀህል አለው። አለምን አየሁት አንድም የሚረባኝን አላገኘሁበትም በውስጧም ያሉት በፍጥነት ይጠፋሉ አለው። አባቱም ጥቂት ቆይ አላቸው እንደ ተስፋው ፫ አመት ፈተነው ከ፫ አመትም በኋላ መነኮሳት በጎ ስራውን አይተው ለመምሐሩ ነገሩት የእንጦስን ስራ የመነኮሳትን ገድል ሁሉ አሳየው። አባ እስትንፋሰ ክርቶስንም አመነኮሰው የቆቡን ፍጻሜ ግን ጻድቅ አባሙሴ ካህንት ከደብረ ድባ ተቀበል አለው። ከዚህ በኋላ የቅስና ማዕረግ ተቀበለ አንድ ቀን ሲፀልይ ጌታችን ለአባ እስትንፋ ክርስቶስ ተገለጸለት ቃል ኪዳን ሰጠው። በቀን በቀን እልፍ እልፍ እምርልሃለሁ አለው በ፫ በአላቱ በተወለድህበት፤ በተጠመቅህበት እና ከሙታን በተነሳህበት ቀን እንደዚህ ፯ ፯ እልፍ እምርልሃለሁ አለው እስከ ምፅአት ዝክርህን ያደረገ ስምሕን የጠራ ገድልህን የፃፈ ያፃፈውን ያነበበውንም የተረጎመውንም እምርልሃለሁ አለው። ከዚህ በኋላ አባታችን እስትንፋሰ ክርስቶስ ጌታን ልደትህ ስንት ነው አለው ፪ ነው። ፫ የሚሉ አሉ አለው። ጌታም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ተወለድኩ ድሕረ ዓለም በዚህ ዓለም ያለ አበት ያለ ዘርዕ ከድንግል ማርያም ተወለድኩ። ራሱ ክቡር ከባሪውም አክባሪው እሱ ነው በል ልጄ እስትንፋሰ ክርስቶስ በጸጋ ፫ ልደት የሚል ቢኖር በእኔ ስልጣን በአንተም ሥልጣን የተወገዘ ይሁን ከ፫ትነቱ አጉድሎ ወይም ፬ተኛ ጨምሮ የሚያስተምር ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ወልደ አብ ወልደ ማርያም እያልክ ለሁሉም ፪ ልደትን ብለህ አስተምር አለው። ከዚህ በኋላ ኃይል ሞልቶት ወደ ሰማይ አረገ። ከዚህ በኋላ አባታችን ጉበረ መንፈስ ቅዱስን ለመገናኘት ወደ ዝቋላ ሔደ ፯ ቀንም ጸለየ በሰባተኛው ቀን አባታችን ጉበረ መንፈስ ቅዱስ ወደ አሳቸው መጡ አባታችን እስትንፋሰ ክርስቶስ እጅ ነስተው የሃይማኖትን ነገር ጠየቋቸው ለነፍስ የሚረባ የሚጠቅም ከእግዚአብሔር ፊት የሚያደርስ አባቶቻችን እና የእኛ ሃይማኖት ምንድን ነው? አሏቸው አባታችን ጉበረ መንፈስ ቅዱስ መለሱ እንዲህም አሉ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፊት የሚደርስ የአባቶቻችንና የሃይማኖት በአካል ፫ በመለኮት ፮ ብሎ ማመን ነው። የወልድ ልደት በእውነት ፪ ነው አስቀድሞ ከአብ ያለ እናት ተወለደ አንድ ልደት ሁለተኛ ከማርያም ያለ አባት ተወለደ ሁለት ልደት ነው ከዚህ ሃይማኖት የወጣ ያጎደለ የጨመረም በእኔም ቃል በአንተም ቃል የተወገዘ ይሁን እላለሁ አላቸው። አባታችንን ተክለ ይማኖትም እደዚህ አሏቸው ከቅዱሳን ቦታ ሃይማኖትን ጠይቀው ይረዱ ዘንድ ከገዳም ወደ ገዳም ይሄዱ ነበር ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ መሸባቸውና ከጎጃም ደብረ አስጋጅ አስኪ ደርሱ ፀሐይን ገዘቷትና ቆመች ከዚህ በኋላ ከደብረ ድባ የቆብ ማዕረግ ተቀብለው የምንኩስናን ስራ በጨረሱ ጊዜ አልተቀመጡም ቆሞ መጸለይን አጸኑ እንጂ ያለቁርባን እህልም አልቀመሱም። ከዚህ በኋላ ዋሻ አነጹ ከረዳቸው ከአባ ልብሰ ክርስቶስ ጋር ገቡ በውስጡም በጾም በጸሎት በመስገድና በመትጋት በመራቆትና በችግር ጌታን አገለገሉ ድውያንን በመፈወስ ነፍስንም ከሲኦል በማውጣት ብዙ ተአምራት አደረጉ በቀን በቀን ሺ፬፤ሺ፬ እልፍ ጸሎት ይጸልዩ ነበር።

ተፈጸመ በእግዚአብሔር ቸርነት አሜን።